# ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ! – አቶ ነሲቡ ስብሃት(አሉላ)

መጽሐፍ “ፍጹም ነው እምነቴ” ቀይ ሽብርና፤ የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ

ደራሲ፡ አቶ ነሲቡ ስብሃት(አሉላ) መስከረም 2007

አስተያየት

በአቶ ክንፈ ኪሩቤል ተስፋሚካኤል(አዲስ አበባ) ጥር 2007 ዓ.ም

ይህ የአቶ ነሲቡ ስብሃት መጽሐፍ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ የስራ ውጤት ነው፡፡ በ 1970 ዓ.ም “በቀይ ሽብር” ስም ያለ ፍትሕ ስርዓት ስቃይና መከራ ለተቀበሉት፤ ለአካል ጉዳተኛነት ለተዳረጉት፤ ለስነ ልቦና ጉዳት ሰለባ ለሆኑት፤ ለተሰደዱት፤ ውድ ልጆቻቸውንና ወላጆቻቸውን እስከ ፍጻሜው በሞት ላጡት ኢትዮጵያውያን ታላቅ መታሰቢያ ነው፡፡ መጽሐፉን ልዩ የሚያደርገው ስለ “ቀይ ሽብር” የተጻፈ እውነተኛ ታሪክ መሆኑ ብቻ አይደለም፡፡ በ 1969-70 ዎቹ የነበረውን የፖለቲካ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን፤ የፀሐፊውን የግል ሕይወት፤በካዛኢንችስ በወቅቱ የነበረውን የወጣት ሁኔታ ይዳስሳል፡፡ ታሪክነቱ በአንድ የአዲስ አባበ ከተማ በከፍተኛ 15 ውስጥ የተካሄደ ቢሆንም፤ድርጊቱን በመላው የኢትዮጵያ ከተሞችና ገጠሮች “በቀይ ሽብር ይፋፋም” መፈክር ስር ወታደራዊ ደርግና በዙሪያው የተሰባሰቡ ስልጣን ፈላጊ ምሁራን በቅንብር ያካሄዱትን ዘግናኝ የግድያ ድርጊት ትዕይንታዊ በሆነ መልኩ ያሳያል፡፡

አንባቢው ሊገነዘበው የሚገባው ይህ ዕልቂት በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደተደረገና በዚህም ከ 1940-1960 ዎቹ የተወለደ አንድ የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ በጅምላ ዕልቂት ማለፉንም ጭምር ነው፡፡

መጽሐፉ በተጨማሪ የሚዳስሰው የታመቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶት በድንገት 1966 ዓ.ም በመቀጣጠሉ የተነሳ በወቅቱ የሕዝቡን የለውጥ ፍላጎትና ብሶት በተደራጀ የፖለቲካ አመራር ሊመራ የሚችል የፖለቲካ ፓርቲ ባለመኖሩ ወታደራዊ ደርግ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ስልጣን በሃይል መንጠቁንና የሕዝብን ዲሞክራሲ መብቶች መግፈፉና የግፍ አገዛዙ የኢጣሊያን ፋሽስቶች ኢትዮጵያን በወረሩበት ዘመን ከፈጸሙት ያላነሰ መሆኑን ያነፃፅራል፡፡

ሌላው መጽሐፉ አንባቢውን የሚያስገነዝበን የማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም እናራምዳለን የሚሉ ምሁራኖች በተከተሉት የፖለቲካ መስመር ልዩነቶች የተነሳ መቻቻልና መደማመጥ በመጥፋቱ በሃገሪቱና በሕዝቦቿ ላይ የደረሰውን ጥፋት ነው፡፡ በተለይ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ(መኢሶን) የተባለ ቡድን ደርግን ወግኖ ስለመቆሙ፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ) ደግሞ ደርግን ኮንኖ የራሱን አቋምና መስመር ስለመከተሉ፤ ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ነጻነትና እኩልነት በጽኑ ስለመቆሙና ስለመታገሉ ያስረዳል፡፡ በዚህም የተነሳ በለጋ ወጣትነት ዕድሜያቸው የኢሕአፓን መስመር በፍጹም እምታቸው የተከተሉት ወጣቶች በኢሕአወሊ ድርጅታቸው ስር ያካሄዱትን የመረረ ትግልና የተቀበሉትን መስዋዕትነት በግልጽ ያሳያል፡፡

አቶ ነሲቡ፤ የኢሕአፓን የሕዝብ ፓርቲነትን አበክረው ገልጸዋል፤ ሆኖም ትግሉ እየመረረ በሄደበት ወቅት መኢሶን፤ ወዝ ሊግ፤ ማሊሬድ፤ ኢጭአት በተባሉ የድርጅት ካድሬዎችን በመጠቀም ወታደራዊው ደርግ በቀይ ሽብር ስም ድርጅቱን የመምታቱ ሃይል በተፋፋመበት ወቅት በኢሕአፓ ድርጅት ውስጥ መከፋፈል ስለመከሰቱ፤ መዋቅሩ ስለመዘበራረቁና መፈራረሱ፤ መክዳትና ከደርግ ጋር መሰለፍን ስለማስከተሉ፤ በከተማው ትጥቅ ትግል የተነሳ ስህተቶች ሰለመፈጸማቸው በግልጽ አስቀምጠውታል፡፡ ይህም ሚዛናዊነታቸውንና እውነተኛነታቸውን ያሳያል፡፡ የሕቡዕ ድርጅታዊ አሰራር በውስጡ አለመተማመንና መከፋፈል ከተፈጠረ ጉዳቱ ቀላል እንደማይሆን ያስተምራል፡፡

ካድሬ ከፈለኝ ዓለሙ እንደ ምሳሌ ቀረቡ እንጂ፤ በአጠቃላ የደርግ ካድሬዎችን ጨካኝነት የአውሬነት ባሕሪይ በግልጽ ያሳያል፡፡ የኢትዮድያ ሕዝቦች የሚታወቁበት ሃይማኖታዊነት፤ ሰብዓዊነት፤ ታጋሽነት፤ ሩህሩህነት ወዘተ የመሳሰሉትን ታላላቅ ባሕሪያት ፈጽሞ የተቃረነ መሆኑን ይገልጻል፡፡ “ሁሉም ያልፋል” የሚለውን ብሂል ፈጽሞ የዘነጉ፤ ጊዜያዊ የበላይነታቸውን እንደ ዘለዓለማዊነት አድርገው የቆጠሩ፤ በግፍ ያፈሰሱት ደም ጊዜው ይዘግይ እንጂ እንደሚፋረዳቸውና ተገቢውን ፍርድም እንደሚሰጣቸው መጽሐፉ ዋቤ ሰጥቶአል፡፡ ይኸውም ማንነቱን ቀይሮ አሜሪካ የገባው ከፈለኝ ዓለሙ በዴኒቨር ኮሎራዶ ተይዞ  ከ 36 ዓመታት በኋላ የተሰጠውን የ 22 ዓመታት ፍርድ ስንመለከት ለሌሎችም ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ አይሁዶችን የጨፈጨፉ የናዚ ሂትለር መንግሥት ሰዎችም እንዲሁ አላመለጡም፡

ከ 1980 ዓ.ም በኋላ እና በኢሕአዴግ ዘመን የተወለደው ወጣት ትውልድ ከሞላ ጎደል የኢትዮድያ ሕዝቦች ከድህነት፤ ከበሽታ፤ ከረሃብ ከብሔር ጭቆና ተላቀው ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመስረት ስላደረጉት ትግል ባይተዋር ይመስላል፤ አለያም ስለ ተካሄደው ትግል እምብዛም አያውቅም ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አሁን ያለው ይህ ወጣት ትውልድ የቀደመው ያ ትውልድ ስለከፈለው መስዋዕትነት ከአቶ ነሲቡ ስብሀት መጽሐፍ ግንዛቤ እንዲወስድ ያስችለዋል፡፡ የዚህ ዘመን ወጣት ጉዳዩን መገንዘብ ብቻ ሳይሆን ይህንን የመሰለ ድርጊት በድጋሚ እንዳይከሰት የቀደመ ታሪኩን ማወቅ፤ መዘጋጀትና መጠንቀቅ ይገባዋል፡፡

ባለፉት 23 ዓመታት የተወለደው የአሁኑ ትውልድ ማንነቱንና ምንነቱን ወደፊትስ አቅጣጫው ምን መሆን እንዳለበት ከወዲሁ መገንዘብ የሚኖርበት ዘመን ላይ ተደርሷል፡፡ ታላቅ የነበረ ሕዝብ ወደ ጥንቱ የታላቅነቱ መሰረት እያመራ መሆኑን ማጤን ጊዜው አሁን ነው፡፡

በ 1966 ዓ.ም አብዮት የዲሞክራሲ መብቶቹን ሊቀዳጅ የነበረ ሕዝብ  በወታደራዊው ደርግ መብቶቹን በመነጠቁ የተነሳ መብቱን ለማስመለስ የኢትዮድያ ብሔር ብሔረሰብ ወጣቶች በቀጣይነት በየድርጅታቸው ረጅም ከገጠር የትጥቅ ትግልን ለማካሄድ ወስነው በከፈሉትን መስዋዕትነት ደርግን በ 1983 ዓ.ም ከስልጣን ለማስወገድ በቅተዋል፡፡

በዚህ አጋጣሚ ለዚህ አስተያየት አንባቢዎች ለማሳወቅ የምፈልገው “ ኢሕአፓ እና ስፖርት ” እውነተኛ ታሪክ በሚል ርዕስ በገነነ መኩሪያ(ሊብሮ) 2005 ዓ.ም የተጻፈው መጽሐፍ አቶ ነሲቡ ያቀረቡትን መረጃ የሚያጠናክር ሆኖ አግንቼዋለሁ፡፡ ፈልገው ያንብቡት፡፡

ከንፈ ኪሩቤል ተስፋሚካኤል(አዲስ አበባ) ጥር 2007 ዓ.ም